

# ዓለም ፀሐይ ወዳጆ ተሸለመች!

ባለፈው ቅዳሜ ስምፕምበር 6/2014 በጀርመን ፍራንከፈት የሚገኙ ኢትዮጵያውያን አርቲስት ዓለም ፀሐይ ወዳጆን በመሸለም አከበሯት። የኢትዮጵያ ናሽናል አርት ካውንስል (The Ethiopian National Arts Council - ENAC) በመባል የሚታወቀውና በጀመርን የሚገኘው ድርጅት በሚያደርገው ዓመታዊ ዝግጅቱ አርቲስት ዓለም ፀሐይ ወዳጆን የዓመቱ ተሸላሚ አድርጓል።

የድርጅቱ መስራችና ሥራ አስኪያጅ አቶ ተፈሪ ፈቃደ ለዘኢትዮፆያ ጋዜጣ እንደገለጹት ካውንስሉ የኢትዮጵያን እውቅ የኪነጥበብ ባለሙያዎች በተለይም በኢትዮጵያ የሚገኙትን አንጋፋ አርቲስቶችን ለመንከባከብና ድጋፍ ለመስጠት ጭምር የተቋቋመ ነው። ካውንስሉ በየዓመቱ ከጳጉሜ 1-5 ድረስ አርቲስቶች እንዲከበሩና በመጨረሻው ቀን ጳጉሜ አምስት ደግሞ በልዩ ዝግጅት እንዲታሰቡ ያደርጋል። የዓመቱንም ተሸላሚ አርቲስቶች ይመርጣል። ለምሳሌ ባለፈው ዓመት ሎሬት ጸጋዬ ገ/ መድህንን ሸልሟል፡፡

በዘንድሮው ዝግጅቱም አርቲስት ዓለም ፀሐይ ወዳጆን በመሸለም በህይወት ታሪኳና በጥበባዊ ሥራዎቿ ዙሪያ የተቀናበሩ ዝግጅቶችን አቅርቧል። በተለያዩ በተለይም በኢትዮጵያ የሚገኙ እንደ መርዓዊ ስጦት፣ ጌታቸው ደባልቄ፣ ተስፋዬ ገሠሠ፣ ደበበ እሸቱ፣ ጌትነት እነየው፣ የመሳሰሉ አርቲስቶች ስለ አርቲስት ዓለም ፀሐይ የሰጡትን ምስክርነትና አድናቆት በአዳራሹ ለነበሩ እንግዶች አቅርቧል። በአካል ተግኝተው የየራሳቸውን አድናቆት የገለጹላት ግለሰቦችም ነበሩ።

አቶ ተፈሪ እንደገለጹት ከካውንስሉ በተጨማሪ፣ ሌሎች ሁለት ድርጅቶች የየራሳቸውን ሽልማቶች አበርክተውላታል። ስቱትጋርት የሚገኘው የኢትዮ ብሪጅ ኢትዮጵያውያን ማህበርና ኑረምበርግ የሚገኘው "እንደ ዜጋ የኢትዮጵያውያን መረዳጃ ማህበር" አድናቆትና ክብራቸውን በሽልማት አጅበዋል።

እውቋ ገጣሚ በእውቀቱ ስዩምና አርቲስት ሐረገወይን አሰፋም ከኢትዮጵያ ተጋብዘው በክብር እንግድነት ተገኝተዋል። የስነጥበብ ሥራዎቻቸውን ማቅረባቸውና ለዚህም አድናቆ የተቸራቸው መሆኑን አቶ ተፈሪ ገልጸዋል።

በጀርመን ነዋሪ፣ የአፍሪካና የመካከለኛው ምስራቅ ጉዳዮች አማካሪና፣ የካውንስሉ የበላይ ጠባቂ የሆኑት የልዑል አስራተ ካሳ ልጅ ልዑል ዶ/ር አስፋው ወሰን አስራተ፣ ለአርቲስቷ የተዘጋጀውን ሽልማት ማበርከታቸውም ተገልጿል። ከኢትዮጵያ ደራሲ አያልነህ ሙላት እንዲሁም ታዋቂው የሙዚቃ አቀንባሪና ተጫዋች ዳዊት ይፍሩን ጨምሮ ሌሎችንም በአባልነት የያዘው ካውንስሉ እድሜና ኑሮ ያደከማቸውን፣ አንጋፋ የኢትዮጵያ አርቲስቶች መርጃ የሚሆን ገቢ የማፈላለግ ሥራም እንደሚሠራ ገልጸዋል። የዚህ አካል በሆነው ዝግጅትም ላይ የተለያዩ የፋሽን ትርኢቶችና የኪነጥበብ ሥራዎች ቀርበዋል። የጣይቱ የባህል ማዕከል መስራችና ሥራ አስኪያጅ ዓለም ፀሐይ ወዳጆን ለማክበር ከቀረቡት ዝግጅቶች አንዱ የጣይቱ ድራማ እንደነበርም አቶ ተፈሪ አስረድተዋል። ላለፉት 14 ዓመታት በዋሽንግተን ዲሲ በሚገኘው የጥበብ ማዕከል፣ በየወሩ የመጨረሻው ዓርብ፣ በሚሰናዳው የግጥም ምሽት፣ በርካታ የጥበብ ሰዎች ታሪክና ሥራዎቻቸው እንደሚከበሩ ይታወቃል። አርቲስት ዓለምፀሐይ ለተመሳሳይ ዝግጅት ወደሌሎቹ የአውሮፓ አገራት ማቅናቷ ታውቋል። (ዘኢትዮጵያ)